# ተስለክላኪ ዘንዶ

## “ሌላም  አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ”

**“ወእምዝ ወጽአ ካልዕ አርዌ እምነ ምድር፤ ወበሥልጣኑ ለቀዳማዊ አርዌ ይገብር ኵሎ በቅድሜሁ፤  ወይረስያ ለምድር  ከመ እለ ይነብሩ ውስቴታ ይሰግዱ ሎቱ ለቀዳማዊ አርዌ ”** (ራዕይ 13፡12) ።


ከቀሲስ አስተርአየ ሰኔ 6 ቀን 2008

nigatuasteraye@gmail.com  Jun 13, 2015


ሰሞኑን በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ በውስጥና በውጭ የሚካሄደውን አየሁ። የሚንጫጫውንም ሰማሁ። ተጽፎ ባነበብኩትና በመገናኛ ዘዴዎች በሰማሁት ጫጫታወች ውስጥ ያለችውን ቤተ ክርስቲያንን እንዴት ልግለጻት ብየ አሰብኩ። በዚህ የሀሳብ ማእበል ውስጥ ሳለሁ፤  በአባይ በርሀ፤ በፈላው ስር ተከሰተ እየተባለ በልጅነቴ ሲነገር የሰማኋት ቀውጢ ትዝ አለችኝ።  በዚያች ቅጽበት በተከሰተችው  ቀውጢ ክስተት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያኔን አየኋት።

ታሪኩ እንደዚህ ነው:- ሁለት ወንድማማቾች በአባይ ዳር በፈላው ስር ሲሄዱ። ረሀብ አስክሮት የሚያድነውን ነገር እየፈለገ በመቀነዝነዝ ላይ የነበረ የቀትር ዘንዶ ከፈላው ውስጥ ተስለክልኮ ባንዱ ላይ ተጠመጠመበት። የሰውየውና የዘንዶው ሰውነት እንደገመድ ተፈተሉ። ወንድሙ ለተወሰነ ደቂቃ በድንጋጤ ደንዝዞ  ቆመ። በሰውየው ላይ የተጠመጠው ዘንዶው ሰውየውን ለመዋጥ እያደቀቀው ነው።  ዘንዶው በሰውየው አካል ላይ እንደገመድ ሰለተጠመጠመ  በያዘው ነፍጥ ዘንዶውን ከሰውየው ለይቶ መምታት አልቻለም።  ሁለቱንም ደርቦ በመምታት ወንድሙን የሚገድለው ሆነ። በድንጋጤ የሚመለከተው ወንድም መላው ጠፋበት።

የሚያደርገው ጠፍቶት በመጨነቅ ላይ ሳለ፤  ዘንዶው የወንድሙን አካል እያሸና እያደቀቀ ለመዋጥ  በወንድሙ ራስ ላይ አፉን ለመትከል ሲጀመር ሲል፤ ዘንዶውን ከሰውየው ለይቶ ለመምታት ነፍጠኛው ወንድም እድል አገኘ። ለመዋጥ በከፈተው በዘንዶው አፍ የነፍጡን ጫፍ  አስተካክሎ  ከተተው። አፈሙዙን በዘንዶው ምላስ አንተሮስ ጥይቱን በዘንዶው ላንቃ ለቀቀበት።  የዘንዶውን ራስ በታተነው። ዘንዶው ኃይሉ ፈረሰበት። በሰውየው አካል ተጠምጥሞ የነበረው ዘንዶ ተተረተረና ለቀቀው። ዘንዶው ሞተ። ሰውየው

ተረፈ። ልጅ ሆኘ ሲነገር ስለሰማሁትና ቅኔም ስለቆጠርኩበት፤ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና እና በኢሀደግ መካከል ያለውን ሁኔታ ሳስብ ይህች አስጨናቂ ክስተት ትዝ አለችኝ።

ባለ ራዕዩ " **ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ**" (ራዕ 13፡) እንዳለው፤ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን እያደቀቀ ለመዋጥ የተለያዩ አውሬዎች መልካቸውንና አቅጣጫቸውን እየቀያየሩ ብቅ ሲሉ አየኋቸው።

ምንም እንኳ "አናቅጸሲኦል ኢይሄይልዋ" ሲል በተናገረው በክርስቶስ ኃይል ቤተ ክርስቲያን የማትዋጥ መሆኗን ባምንም፤ ዶክተር አረጋዊ በርኄ ከዚህ በታች በምጠቅስላቸው ምስክርነታቸው እንደገለጹት፡-

"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።"

ብሎ ከበርሀ ተመዝግዝጎ (ተስለክልኮ) የመጣው ወያኔ፤ በኢትዮጵያ ላይ ተጠምጥሞ እያደቀቀ ቤተ ክርስቲያንን ሊውጥ የከፈተውን አፉን ተመለከትኩ። **"ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ" (ራእ 13፡11)** እንዳለውም ከነአቶ ታምራት ላይኔ ጋራ በተባበሩት ጳጳሳትንና ቆሞሳት ጀርባ እየታዘሉ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የገቡት ሌሎችች ዳንዔል ክብረትን የመሳሰሉትን አውሬዎች እየተስለከለኩ ከተጠመጠሙባቸው ሰዎች ለይቶ ለማቅረብ ከፊላው ነፍጠኛ የበለጠ ጥበብ የሚጠይቅ ሆኖ ተሰማኝ።

ሊቃውንት አበው "ጥበብ እንተ ይእቲ ትሄይስ እምዕንቁ ክቡር ወኩሉ ክብር ኢመጠና፤ ላቲ ምክር፡ ወእዘዝ፡ ጽንዕ፡ ወአዕምሮ ወባቲ. . . ኃያላን ይጽሕፉ ጽድቀ" በሚለው ምንባባ ላይ በሚሰነዝሩት ድርብ ሀተታቸው፡- "ነፍጥ የተሸከመና ተኳሽ ሁሉ ነፍጠኛ አይባልም። ነፍጠኛ ለመባል ወይም ከነፍጠኛ ደራጃ ላይ የሚያደርሰው፤ በሚተኩሳት ጥይት ተሰለክልኮ የተጠመጠመውን፤ ከተጠመጠመበት ነገር ለይቶ መምታት ከሚያስችለው ትኩረት ላይ ሲደርስ ነው። ብእር ቀርጾ ብራና ፍቆ ቀለም በጥብጦ የሚጽፍም፤ የዘንዶ ባህርይ ያለውን ሰው ተሰልክልኮ ከተጠመጠመበት ለይቶ የማቅረብ ብቃት ከሌለው ጠልሰመኛ እንጅ ጸሐፊ አይባልም" ብለው የሚያቱትም ትዝ አለኝ።

ብቃት ችሎታና እውቀቱ ሳይኖራቸው በቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን ሥጋዊ ነገር ለመዋጥ እየተስለከለኩ በተሰገሰጉት አስመሳዮች ጳጳሳትንና ቆሞሳት ጀርባ እየታዘሉ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የገቡትን እንደ ዳንዔል ክብረትን የመሳሰሉትን ተስለክላኪ አውሬዎች፤

በቅዱሳን ስም ተደራጅተው በንጹህ ህሊና ለቤተ ክርስቲያናቸው ቆመው ከሚታገሉት ንጹሐን ኦርቶዶክሳውያን ሰዎች፤ ለይቶ ለማቅረብ ከምድራዊ ጥበብ የራቀ ሰማያዊ ጥበብ የሚጠይቅ ሆኖ ተረድቸዋለሁ።

ባካባቢው ተደብቆ ያገኘውን እየዋጠ ራሱን ለመቀለብ ከሚውጠው ባሻገር እግዚአብሔር ይፈርድብኛል ሰው ይነቃብኛል ብሎ የማያስብ በፊላውና በረግረጉ መሬት ራሱን ደብቆ እያደነ ከሚውጠው ተስለክላኪ ዘንዶ የተሻለ አዕምሮ እንደሌለው ተረድቸዋለሁ። በውስጡ የሚስለከለክበትን ህዝብ ፊላ፤ ድርጅቱም ረግረግ አድርጎ ለራሱ ህልውና ብቻ እየተጠነቀቀ ሰው የሚጎዳ ሁሉ፤ የዘንዶ ተስለክላኪ ባህርይ ያለው በዘንዶ ጥበብ የሚመራ ነው። ይህ መሳይ ባህርይ የተስለከለከበትና የሚስለከለክበትን ቀዳዳ ሁሉ እያሳየሁ ለመዝጋት፤ ለኔ አድካሚ እንደሆነብኝ፤ ያንባቢን ትኩረትና ትእግስት የሚጠይቅ መሆኑን ማሳሳብ እወዳለሁ።

ታላቁ ተስለክላኪው ዘንዶ ወያኔ በከፈተው በር ወደ በቤተ ክህነቱ ከገቡት፤ በነጋ በጠባ "እግዚኦ እለ ንስእለከ ኢንሰተት አላ በስክየት ነሀሉ ዲበ ጸላኢነ" ኪዳን ዘነግህ) እያልን የምንጸልየውን ሰምተው ከማያውቁ ተስለክላኪ እባቦች ዳንዔል ክብረት አንዱ ሆኖ አይቸዋለሁ።

አባቶች "እግዚኦ እለ ንስእለከ ኢንሰተት አላ በስክየት ነሀሉ ዲበ ጸላኢነ" የሚለውን ሲተረጉሙ፤ ሰው በሰውነት መስፈርት የሚለካው ሰው ሆኖ በመታየቱ ብቻ አይደለም። ራሱ የሚያስነቅፈውን ነውር እየሰራ በሰራው አስነቃፊ ነገር ሌላውን የሚነቅፍ ሰው፤ የማያስብ ተስለክላኪ ዘንዶ ነው። ከእንዲህ ያለ ተስለክላኪ ዘንዶ መሳይ ባህርይ ሰውረን ይሉና፤ ሰው ማለት እንደ ቅዱስ ጳውሎስ "ወንድሞቼ ሆይ እኔ እስከዚህች ቀን ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ በመልካም ህሊና ኖሬአለሁ " (የሐ 23፡1) እያለ፤ በተከሰሰበትና በሚከሰስበት ጉዳይ ከህሊናው ክስ የነጻ መሆኑን በተግባሩና በቃሉ ለማሳየት የበቃ ህሊና ያለው ነው" ይላሉ። ከዚህ ቀጥየ ዲያቆን ዳንዔል ራሱ በሚከሰስበት ነገር፤ **"ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"** እያለ ራሱን ስልክልክ ዘንዶ አድርጎ ወደ አቀረበበት ዝርዝር ሀተታ እሻገራለሁ።

## "ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"

እንደ ጠንቋይ ብእራቸውን አነሱ እያለ አቡነ ማትያስን የሚዘልፍበትን ይህን ጉዳይ ዲያቆን ዳንዔል ክብረት፤ በአክራሪነት እየሰበከ፤ እኛን እርስበርሳችን አደባድቦበታል። በኦሬንታሎችና በባዛንታዮኖችን ቤተ ክርስቲያናችንን አስነቅፎበታል። ራሱ ያደረገውን

እያወቀ፤ እንደማያውቅ ሆኖ ዛሬ **"ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"** እያለ ከ11 አመታት በኋላ ብቅ ማለቱ ፤ ወያኔ በቤተ ክርስቲያን ከከተታቸው "**ሌላ አውሬ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ ያየሁ" መሰለኝ።**

በቤተ ክርስቲያናችን ህግና ስርአት የነገረ መለኮት ተመራማሪም ሆነ ጸሐፊ ነኝ የሚል፤ እኛ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ከኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት የምንለየው በዜማችን በቅኔያችን በመልክአ ምድራችን በቋንቋችን በደም ግባታችን እንጅ፤ በነገረ መለኮት አንድ መሆናችንን መረዳት አለበት። በዜማ፤ በቋንቋ፤ በመልክአ ምድርና በምድራዊ ዜግነት ሁሉም አንድ እንዳይደሉ ማወቅ ይገባዋል። ይሁን እንጅ ከቅኔ ቤት ጀምረን እስካንድምታው ድረስ የምንደክመው የምንለያይበትንና አንድ የምንሆንበትን አውቀን ሚዛኑን ጠብቀን ከኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ለማስረከብ ነው። **ይህንን ያልተረዳና ያልተገነዘበ ከሰንበት ተማሪነት አልፎ፤ ለነገረ መለኮት ምስክር፤ ተመራማሪና ጸሐፊ ነው ሊባል አይገባውም።**

ይህንን ሳይማሩ ሳይገነዘቡና ሳያውቁ ወያኔ በሰበረው በር ዘው ብለው ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ገብተው በዚህ ጉዳይ ከኦሬንታልሎች ጋራ እንደማንገናኝ ከሚያተራምሱት አንዱና ዋነኛውን ዛሬ "ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ" እያለ በአቡነ ማትያስ ላይ በማሾፍ መልክ ያቀረበው ዲያቆን ዳንዔል ነው።

ዛሬ ራሱ ዲያቆን ዳንዔል በነገረ ዘርቅ ያቀረበውን በዚህ ጉዳይ ለ10 አመታት በተደጋጋሚ የቀረቡትን ጦማሮች የተለያዩ ድረገ ገጾች ያቀርቧቸው ስለነበር፤ የኢትዮጵያ ነገር የሚያሳስበው ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ውጭ የሆነ ሁሉ ዜጋ፤ ስለ አገሩ ወቅታዊ የሆነ ነገር ለማግኘት ድረ ገጾችን ሲፈትሽ፤ እግር መንገዱን ይቃኛቸው ስለነበር፤ ዲያቆን ዳንዔል ይህንን ጉዳይ በአክራሪነት ይሰብከው እንደነበረ ያውቀዋል።

**"ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"** እያለ እራሱን ለነገሩ እንግዳ አድርጎ በነገረ ዘርቅ ሲያቀርበው፤ እራሱ የሚከሰስበትና የሚወቀስበት እንደሆነ በቅርብ የምናውቅ ዝም ብለን ማለፍ ስርየት የሌለው በደልና በተመልካችም ዘንድ የሚያስገምት ሆኖ ተሰማኝ።

በዚህ ጉዳይ በሰራው በደል ይቅርታ ሳይጠይቅ ንስሀ ሳይገባ **"ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"** እያለ በነገረ ዘርቅ ማቅረቡ_ እስካሁን በጻፋቸው፤ ወደፊትም በሚጽፋቸውና በሚናገራቸው ነገሮች እንዳይታመን የሚያደርገው እንደሆነ የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም።

***“ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?”*** *እያለ በነገረ ዘርቅ ያቀረበውን ጉዳይ አባ ሠረቀ* **“እውነትና ንጋት”** *በሚል ርዕስ ሰብስበው በማሳተም፤ በመንፈሳውያን ተቋማት ዙሪያ ያሉትን ታዛቢዎች ጋብዘው፤ በቤተ ክህነቱ አደባባይ ያስመረቁት መጽሐፍ ከሞላ ጎደል ሰብስቦ ይዞታል። ምንም እንኳ አባ ሰረቀ በስማቸው ቢያሳትሙትም፤ በዚህች መጽሐፍ ግማሽ ላይ የሰፈሩት ያባ ሠረቀ የራሳቸው ድርሳናት አይደሉም። ዲያቆን ዳንዔል በአቡነ ማትያስ ስምና ፊርማ ፤ ራሳቸውን አቡነ ማትያስን ከማህበረ ካህናቱን ጋራ የወጋበትንና ያስወጋበትን ጠልሰም ከሞላ ጎደል አካቶ የያዘ ነው።*

*ዲያቆን ዳንኤል ካዲስ አበባ እየተመላለሰ፤ ከዋሽንግተን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እየተንደረደረ፤ የውጩን ሲኖዶስ ደበደብኩ እያለ የፖለቲካና የሃይማኖት ጠበቃ ሆኖ ራሱን ያቀረበበት የነ አቡነ ጳውሎስን ቀልብ የሳበበት ይህ ጉዳይ እገዳ እንጅ ውግዘት አልንበረም። ውግዘት እንኳ ቢሆን መመሪያችን ከሚጠይቀው ቁጥርና ስብሰባ መጠን በላይ በታላላቅ አካላት፦*

*1ኛ፦በማህበረ ካህናቱ ጉባዔ ታይቶ የተሰነዘረው እገዳ ትክል እንዳልሆነና ይልቁንም እንዲታረም ወስኖ ለሚመለከተው ልኳል።*

*2ኛ፦የቤተ ክርስቲያኒቱ መስራች የነበሩት አቡነ ይስሀቅ በማህበረ ካህናቱ የተላለፈውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ እገዳውን አንስተውታል።*

*3ኛ፦ለኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት ቀርቦ፤ ፓትርያርክ ሽኖዳ ወክለው ወደ ከንሳስ በላኳቸው ብጹዕ አቡነ ማቃርያስ አማካይነት ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተው አንስተውታል።*

*4ኛ፦በአባ ሰረቀ እና በነ ዳንዔል መካከል ውዝግብ በተነሳበት ወቅት፤ አባ ሰረቀ በጉዳዩ ይንጸባረቁ የነበሩትን መዛግብት ከሞላ ጎደል ሰብስበው አሳትመው በቤተ ክህነቱ በተመረቀ ጊዜ የተደመደመ ነገር ነው።*

*በመጀመጀመሪያ በጥንታውያን ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ህግና ስርአት አንድ ሰው ብቻውን ክህነት ሊያግድም፤ እገዳ ሊያነሳ አይችልም። ይህን የመሳሰሉ ነገሮች ሲከሰቱ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያደጉ የተከሰሱበት የስነ ምግባር የእምነት ህጸጽ የሌለባቸው ካህናት፤ ከዚህ በታች በብሉይ በሀዲስባ በቀኖና መመሪያችን ፦*

*1ኛ፦ ዘዳ 36፡24__25*

*2ኛ፦ ማቴ 18፡15__19*

*3ኛ፦ 2ኛ ቆሮ 13፡1*

4ኛ፡- ፍ. አ. 5፡205  እግዳው ተነስቷል።

መጀመሪያ በማህበረ ካህናቱ፤ ቀጥሎ  በአቡነ ይስሀቅ፤ በኦሬንታሎች፤ ቀጥሎም አባ ሰረቀ መዛግብቱን አሳትመው በጠቅላይ ቤተ ክህነት አዳራሽ አቅርበውት ሲመረቅ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና መሰረት ለመጨረሻ ተዘግቷል።

ይህ ባይሆን እኔም  የተማርኩትንና  እንድጠብቀውም የተሰለፍኩበትን መርሆ ደፍሬ በመጣስ ወደቅስናው ባልተመለስኩ ነበር። በዚያውስ ላይ ከመሰደብ ከመዘለፍ በቀር በዚህ መሬት ላይ ምን ላተርፍበት? ከዚያ በኋል አቡነ ማትያስ ይህን ሁሉ ከላይ የተገለጻውን የቤተ ክርስቲያናችንን መመሪያ ጥሰው በመሄድ አወገዝኩ ሊሉ ይቅርና እግደው ለምን ተነሳ ብለው የወቀሱትም የከሰሱትም አካል የለም። ከሊቃውንት ጉባዔም ሆነ ከሲኖዶሱ የተሰማ ድምጽ የለም። ይህም የሚያሳየው ከላይ የጠቀስኩትን የቤተ ክርስቲያናችንን መርሆ የሊቃውንት ጉባዔም ሆነ ሲኖዶሱ ማክበሩን ነው።

ይሁን እንጅ አሁን ዲያቆን ዳንዔል ከአቡነ ማትያስ ጋራ በግል ሲጋጭ “**ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?”** እያለ እንዳቀረበው እሱን የመሳሰሉ ተስለክላኪ እባቦች ከሰው ጋራ በግላቸው ሲጋጩ እንደማጥቂያ እያደረጉ ወደ ምእመናኑ ማቅረባቸውን አልተውም። በየቦታውና በተለያዩ ጊዜ የቀረቡትን ትቼ፤ በቅርቡ በዋሽንግተን የተከሰተውና ራሱ ያደረገው በቂ ምስክር ይመስለኛል።

በስህተት የገባ ነውና ይታረም የሚለውን በዲሲ የተካሄደውን ጉባዔ በሰብሳቢነት የመሩት፤ የዲሲ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት የበላይ ጠባቂ ነኝ፤ ሊቀ ሊቃውንት ነኝ የሚሉት አባ ወርቅነህ የጠሉትን ለመጉዳት በዙሪያቸው ያሉትን ደፍተሮች አሰባስበው ባሜሪካ ፍርድ አደባባይ መፈራረጅ አድርገው በቅርቡ ማቅረባቸው ተጨባጭ ማስረጃ ነው።

ራሱ ዲያቆን ዳንዔልም ባሜሪካ ያለውን ህዝብ  እያመሰ፤ የውጩን ሲኖዶስ ደበደብኩ እያለ የፖለቲካና የሃይማኖት ጠበቃ ሆኖ ራሱን ያቀረበበት የነ አቡነ ጳውሎስን ቀልብ የሳበበት መሆኑን ክዶ ፤ አሁን ደግሞ አቡነ ማትያስን ለመጉዳት ሲል፤ በነገሩ እየተሳለቅ ባደባባይ ብቅ ማለቱ ሌላው ማስረጃ ነው።

ሁለቱንም ማለትም ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን ከዋሽንግተን፤ ዲያቆን ዳንዔልን ከኢትዮጵያ  ብቅ ያሉ ተስለክላኪ እባቦች ሆነው እንዲታዩ አድርጓቸዋል።

ዲያቆን ዳንዔልን ለመጀመሪያንና ለመጨረሻ በአካል አግኝቼ ያዩሁትና ያነጋገርኩት፤ ይህ የተሳሳተ ትምህት ሰንቆና ታጥቆ እንደ ኮርማ ወይፈን እያገሳ ሰው የሚያፋጅበት የተሳሳተ ትምህርት  ከቤተ ክርስቲያናችን ታርሞ እንዲወጣ በአቡነ ይስሀቅ ጥያቄ ለመነጋገር

በተሰየመው፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ በመሩት ጉባዔው ለመገኘት ዋሽንግተን ዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በሄድኩበት ወቅት ነበር።

ለእረፍት ከጉባዔ አዳራሽ ወጥቼ በቅጽሩ ዙሪያ ስንቀሳቀስ ዳንዔል ክብረትን ከከፈለኝ ጋራ አገኘሁት፤ አቡነ መልከ ጼዴቅ በእመቤታችን ጥንተ አብሶ አለባት ብለዋልና የተወገዙ ናቸው እያሉ ያሰራጩ ነበር። እኔም "አቡነ መልከ ጼዴቅ እናንተ እንደመትሉት እመቤታችን በግበረ መንፈስ ቅዱስ ተወለደች አይሉም። መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ፤ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ፤ ወትከውኒ እሙ ለእግዚእ" ከሚለው ቅጽበት ወዲህ ንጽህተ ንጹህን፤ ቅድስተ ቅዱሳን ሆነች ይላሉ እንጅ፤ ጥንተ አብሶ አለባት የሚሉ አይመስለኝም። ስለዚህ አቡነ መልከ ጼዴቅ አሉ እያላችሁ ለህዝብ የምታሰራጩት ትክክል አይደለም" ብየ ነገርኩት። እሱም **"ቤተ ክህነቱ ባዶ ነው። የሚያርም የሚገስጽ የለም፤ እኛ የሰጡንን ከመቀበል በቀር ምን ማድረግ እንችላለን?"** አለኝ።

**"ብቃት ኖሯቸው በተገቢው መንገድ የሚመሩና፤ የሚሰጡት አመራር ከቅዱሳት መጻህፍት ያልተዛባ ቢሆን፤ አንተ እንዳልከው ሲኖዶስ የወሰነውን መቀበል ተገቢ ነው። ነገሩ ስህተት እንደሆነ ከገባህና ባመራር ላይ ያሉት ብቃት እንደሌላቸውና እንደተሳሳቱ እያወክ ፤ ለማስተካከል መሞከር፤ ካልተቻለ ጉዳዩን ከማጋጋል መሸሽ እንጅ ስህተቱን እያስፋፋህ፤ የተሳሳቱ ሰዎች በስህተታቸው እንዲገፉ ማድረግ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚፈጠረውን ውድቀት መደገፍ እጽፍ ድርብ በደል እንደሆነና እንዲያቆም ነገርኩትና ተለያየን። እኔም ወደጉባዔው አዳራሽ ተመለስኩ።**

ጉባዔው ቀጥሎ እነ ዲያቆን ዳንዔል የሚያራግቡት ነገር በቅዱሳት መጻሕፍት ሲመረምር፤ በእሙሀይ ብርጀትን ህልም በ1854 ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የገባ፤ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ እምነትና ትምህርት ሆኖ ተገኘ። በጉባዔው ላይ የነበሩት መጋቤ ዓዕላፍ መክብብ፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህና አቡነ ገብርኤል፤ **"አቡነ ማትያስን ከቤታቸው ሄደን ብናነጋግራቸው ይቀላል"** ብለው ከዲያቆ ን ዳንዔል ጋራ ይህን ስህተት ያስፋፋ የነበረውን ከፋለኝ ወልደ ጊዮርጊስ የሚባለውን በቃል መዝጋቢነት አስከትለው ወደ አቡነ ማትያስ ሄዱ። ስህተቱ መቸና እንዴት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንደገባና ምን መደረግ እንዳለበት እየገለጹ፤ ከዚህ የሚከተለውን የመፍትሄ ሀሳብ ለአቡነ ማትያስ አቀረቡ።

**"ይህ የተሳሳተ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናችን የገባው እርሰዎም ቀሲስ አስተርአየም በኢትዮጵያ ባልነበራችሁበት ወቅት ነው። ቀሲስ አስተርአየ ይህን እምነት የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህሮቼ ያስተማሩኝ የሮማ ካቶሊክ ነው እያሉ እንጅ፤ የኛ ነው ብለው አላስተማሩኝም" ብለው አምርረው ቆመዋል።**

**አምርረው የያዙትን አቋም ይተው፤ እገዳውንም ይርሱትና ወደ ከንሳስ ተመልሰው አገልግሎቱን ይቀጥሉ ብንላቸውም፤ ቀሲስ አስተርአየ "ሲኖዶሱ ተሰብስቦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ትምህርት ነው ብሎ ቢወስንም፤ ይታረም እያልኩ እጮህለሁ እንጅ አልቀበለውም፤ እስኪጣራ ድረስ ግን አቡነ ማትያስ አገድኩ ያሉበትን ቃላቸውን አከብረዋለሁ፤ ኪዳን አልሳተፍም " በማለት ጸንተው ቆመዋል። እርሰዎም ያገድኩትን አላነሳም በማለት በያዙት ስህተት ከጸኑ የሚያስከትለው ውዝግብ መቋሚያ አይኖረውም። የተሻለው መንገድና መፍትሄው እርሰዎም ቀሲስ አስተርአየም ከጉባዔው ጋራ በመተባበር እንዲታረም ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ ብቻ ነውና፤ እርሰዎም በመካከላችን ተገኝተው ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመርመር ይተባበሩን"** ብለው እነ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ያቀረቡላቸውን ተገቢ ሀሳብና ጥያቄ አቡነ ማትያስ አልተቀበሉም።

ዲያቆን ዳንዔልም ሆነ ከፈለኝም በልጅነታቸው በቤተ ክርስቲያናችን እንደማነኛውም ክርስቲያን የተጠመቁ፤ ቤተ ክርስቲያናችን ክፍት በመሖኗ ሰብረው የገቡ እንጅ በማነኛውም ያብነቱ ጉባዔ የተሳተፉ ባለመሆናቸው ከከተማ የተማሩትን ነገረ ዘርቅና ስላቅ በአቡነ ማትያስና በማህበረ ካህናቱ መካከል መዝራት ጀመሩ። ባብነቱ ትምህርት መሳተፋቸው ይቅርና በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያደጉ ቢሆኑ ኖሮ፤ "አቡነ ይስሀቅም አቡነ ገብርኤልም የሲኖዶስ አባላት አይደሉም፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህም መጋቤ አዕላፍ መክብብም ከናት ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው አይስሟቸው" እያሉ አቡነ ማትያስን ከማሳሳት ይልቅ፤ በስህተት የገባ ነው እያሉ የነገሯቸውን አቡነ ገብርኤልን እንዲሰሙና እንዲተባበሩ ለሰላምና ለተረጋጋ መንፈስ አስተዋጽኦ ያደርጉት ነበር።

ዲያቆን ዳንዔልና ከፈለኝ በቤተ ክህነቱና በህዝቡ መካከል የቆሙ መምህራን ሆነው ይራወጡ ስለነበር፤ አቡነ ማትያስ እነሱን እየሰሙ የካህናቱን ምክር አልቀበልም በማለታቸው የማህበረ ካህናቱ ጉባዔ **"እስከ ዛሬ ወልድ ዋህድ በማለት አንድ ሆነን ከኖርን ከአራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ያለንን የነገረ ሃይማኖት ትስስር እንዳያስቀርብን ብሎም እንዳይለየን፤ ህዝበ ክርስቲኑንም እንዳይከፋፍል፤ የሰላም ጉዟችንን እንዳያደናቅፍ በቅዱሳት መጻህፍትና በቅድሞ ሊቃውንት እምነትና ግናዛቤ ይታረም"** የሚል ማንንም የማይከስና የማይነቅፍ ተገቢ ሀሳብ ለሚመለከተው አቀረበ።

**በ1854 በ**የእሙሀይ ብርጀተንን ሀልም ወደ ሮማ ካቶሊክ የገባውን እምነት እየደገፈ የማህበረ ካህናቱን ሀሳብ አጥብቆ ይቃወም የነበረው ይኸው ዲያቆን ዳንዔል ክብረት **"ካህናቱ ደግሞ ምን ሥልጣን አላቸው"** የሚለውን ጠልስሞ አቡነ ማትያስን አስፈርሞ በመበተን አቡነ ማትያስን ከካህናቱ ጋራ እንዳይተባበሩ ይልቁንም እንዲጋጩ አደረጋቸው። **"ካህናቱ ደግሞ ምን ሥልጣን አላቸው"** እያለ አስፈርሞ በማህበረ ካህናቱ ላይ ለበተነው ጠልስም፤

ማህበረ ካህናቱ ከዚህ የሚከተለውን በመመለሱ በአቡነ ማትያስና በማህበረ ካህናቱ መካከል የተነሳው ግጭት ተጋጋለ።

**"ማህበረ ካህናቱ የላካቸው ሽማግሌዎች ከቤትዎ ድረስ መጥተው በዚህ ጉዳይ ላይ ከእርሰዎ ጋራ በግልጽ ሰፊ ውይይት እንዳላደረጉ፤ እርሰዎም፤ ይህ ተራ ነገር ሳይሆን የእምነት ጉዳይ ስለሆነ በሽምግልና የሚተው ነገር አይደለም ብምንም ውሳኔየን አላነሳም እንዳሉ ጽፈው ሲያበቁ፤ ማኅበረ ካህናቱ ከእርሰዎ ጋራ በዚህ ጉዳይ ምንም ውይይት እንዳላደረገና እንዳልተነጋገረ አስመስለው፤ ውሳኔያቸው ሁሉ ቀሲስ አስተርአየ የነገሯቸውን ብቻ የተከተሉ ይመስላል፤ በዚያውስ ላይ ቀሲስ አስተርአየ የራሳቸውን ጉዳይ ራሳቸው ሽማግሌ ወይም ዳኛ ሆነው ከማህበረ ካህናቱ መካከል ተቀምጠው ሊወስኑ ይችላሉ?በየትኛው ሕግ ነው?በአንድ ወገን ያለውን የቀሲስ አስተርአየን ብቻ ሰምቶ ከሌላ ወገን ሳይሰማ እንደወሰነ በማስመሰል፤ አጻጻፋቸውም ሆነ ውሳኔያቸው ሁሉ ቀሲስ አስተርአየ የነገሯቸውን ብቻ የተከተሉ ይመስላል" ማለት ምን ማለት ነው?** <u>**በስመዎስ ፈርመው የበተኑት ጽሑፍ ይክዳሉን**</u>?እያለ <u>የማህበረ ካህናቱ ጉባዔ</u> በመጻፍ፤ <u>ዲያቆን ዳንዔል በስማቸው ላሰራጨው ጠልሰም</u> እንዲመልስ ተገደደ። እውነትና ንጋት በሚል ርእስ አበ ሠረቀ ባሳተሙት ገጽ 38 ላይ ይመልከቱ።

**"ቀሲስ አስተርአየ ይህ የዛሬ ሃያ (20 )አመት በኛ ቤተ ክርስቲያን ሰርጎ የገባ እንጅ፤ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት አይደለም፤ ሲኖዶስ እርስ በርሱ የሚደባደብ ነው። አገር የካደና የናደ ነው። ስንኳን ዶክትሪን ሊያስጠብቅ ሀገርን ማስጠበቅ ያልቻለ ነው"**እያለ ጠልሰሞ በማስፈረም መበተኑን ሰውሮ፤ በነገረ ዘርቅ ማቅረቡ፤ዮሐንስ ከምድር ሲወጣ አየሁት ያለውን አውሬ መሰለኝ። (እውነትና ንጋት ገጽ 41 )

አቡነ ገብርኤልም፤ በወቅቱ ልደታ ለማርያም በሚል ስም እየታተመ በዋሽንግተን ዙሪያ ይሰራጭ በነበረው ጋዜጣ ላይ "በምሥጢረ ሥላሴና ሥጋዌና ትምህርት ከእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንድ እንደሆን ሁሉ በትምህርተ ሚሪዮሎጅም (ስለ ድንግል ማርያም እምነትና ትምህርት) ከእስክንድርያው ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መለየት የሚያስከትለው ውጤት ከኦሬንታል አብያተ ክርስቲያናት መለየት ይሆናል" ብለው ተቆጥተው እንዲጽፉ ያደረጋቸው ይኸው የዳንዔል ሽፍጥ ነበር። እውነትና ንጋት ገጽ 67 ይመልከቱ።

ዳንኤል ክብረት ይህ እምነትና ትምህርት አዲስና በቅርቡ በቤተ ክርስቲያናችን የተዘራ እንክርዳድ እንደሆነና በጥንቱ የተተካ፤ እሱን የመሰሉ ጠልሳሚዎችም በጥንት ሊቃውንት እግር የተተኩ እንደሆኑ **"በሞት የለዩት ሊቃውንት በሊቃውንት የተተኩ መሆናቸውን፤ በህይወት ያሉትም የቀድሞዎቹን ጽሑፎች የሚተኩ ሌሎችን መጻሕፍት ጽፈው ያበረከት**

**መሆናቸውን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ይመስላል”** እያለ ጠልስሞ አቡነ ማትያስን አስፈርሞ ጥር 18 ቀን 1997 ዓ/ም በተነ። (እውነትና ንጋት ገጽ 42 ይመልከቱ) በዚህ ድፍረቱ ማህበረ ካህናቱ እጅግ አዘነ።

አንድ ጳጳስ በስህተት ክህነት ያዝኩ ቢል፤ ራሱ ጳጳሱ ከክህነት እንደሚወገድ ምንም ግንዛቤ የሌለው ዲያቆን ዳንዔል **“የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ያሳለፈውን የነገረ ሃይማኖት ውሳኔ፤ ወደታች ተመልሶ በማህበረ ካህናቱ እንዲታይ ሊደረግ የቻለበት የይግባኝ ሰሚነቱን ሥልጣን ከየት አገኘው? በየትኛው ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው?የሚለውን ሀሳብ ፈጥሮ ጠልስሞ አቡነ ማትያስን አስፈርሞ በተነ።**

ማህበረ ካህናቱ “**በዚህ አባባልዎ አንድ ጳጳስ እንደፈለገው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የጻፏቸውን መጻህፍትና ቤተ ክርስቲያናችን ለረዠም ዘመናት አምናበት የኖረችውን እምነት መሻር መለወጥ ይችላል ማንም ሊቃወመው አይገባም ማለተዎ ነውን?** በማለት በቀኖና መጽሐፋችን በአንቀጽ 5፡ቁ 157 ላይ የሰፈረውን በመጥቀስ እንዲመልስ ያደረገው የዲያቆን ዳንዔልና የከፈለኝ ተስለክላኪነት ነበር። እውነትና ንጋት ገጽ 50 ላይ ይመልከቱ።

ከላይ እንዳልኩት በአቡነ ማትያስ ስምና ፊርማ እየተጠለሰመ በማህበረ ካህናቱ ላይ የሚበተነውን ያዘጋጁት የነበሩት ከፋለኝና ዲያቆን ዳንዔል ናቸው። ለአቡነ ማትያስ ማህበረ ካህናቱን ይመለስ የነበረውን የሚጠለስመው የካህናቱ ቃለ ጉባዔ መዝጋቢ የነበረው ደግሞ ከፈለኝ ነበር። ዲያቆን ዳንዔል በአካል በጉባዔው ባይገኝም፤ በከፈለኝ በኩል የጉባዔውን ሂደት ይቆጣጠር ነበር። ከፈለኝ በቃለ ጉባዔ መዝጋቢነቱ እኛ ያልሰማነውን ሁሉ አቡነ ማትያስ እንዲህ ብለዋል እያለ ነገሮችን በማከረር ቃለ ጉባዔውን ይቀርጽ ነበር። ከፋለኝ ማህበረ ካህናቱ ለአቡነ ማትያስ የሚሰጠውን ምላሽ እየጻፈ፤ እንደገና በተቃራኒው ከዳንዔል ጋራ ወደ አቡነ ማትያስ እየሄደ በአቡነ ማትያስ ስምና ፊርማ ከካህናቱ ጋራ የተጋጩበትን ያቀናብር ነበር። ይህንም እራሳቸው አቡነ ማትያስ ይግለጹት። ዲያቆን ዳንዔል ሌላም የማይረሳ እጅግ የከፋ ደባ ፈጽሟል።

**አቡነ ማልከ ጼዴቅን ማርያምን ካዱ እያለ** ባሜሪካ ያሳድድበት በነበረው ወቅት፤ በአገር ውስጥም ሟቹን መጋቤ ብሉይ ሰይፈን ያሳድዳቸው ነበር። መጋቤ ብሉይ ሰይፈ የሊቃውንት ጉባዔ ሊቀ መንበር ስለነበሩ ለእርቅ ድርድር ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ አብረን ለመቆየት እድል በማግኘቴ ይህንና የመሳሰሉትን ችግሮች አንስቼ ለጠየኳቸው በሰጡኝ መልስ፤ ዲያቆን ዳንዔል የሰራውን ማይረሳ ደባ ከዚህ በታች የምጠቅሰውን ነግረውኛል።

**“ስለነገረ መለኮት ምንም ግንዛቤ የሌላቸው ሴቶችም ወንዶችም ወጣቶች አምስት ስድስት እየሆኑ በየቀኑ ከቢሮየ በመምጣት አንተ መናፍቅ፡ የሊቃውንት ጉባዔ መሪ ልትሆን**

ይቅርና የቤተ ክርስቲያኒቱ አባል ልትሆን የማይገባህ፡ የተወገዝክ ነህ እያሉ እየተፈቡኝ ይሄዳሉ። እነዚህን ወጣቶች፤ አሜሪካ ድረስ እየመጣ እናንተን በማሳደድ ላይ ያለው የዲያቆን ዳንኤል ደቀ መዛሙርት ናቸው“ ካሉኝ በኋላ መገቤ ብሉይ ሰይፈ በዲያቆን ዳንዔል ላይ የነበራቸውን ምሬት በመቀጠል፤ “ይህን እንዲያካሂዱ እነ ዲያቆን ዳንዔልን የሚያበረታታና የሚያደፋፍር ኃይል እንዳለ ጥርጥር የለውም። በሉ የሚላቸው ኃይል ከጀርባቸው ባይኖር ይህን ያህል ድፍረት አይኖራቸውም ነበር።

አንተ ግን ምንም እንኳ ካንተ ጋራ አብረው የተሰለፉት አቡነ ይስሀቅ በሞት ቢለዩህ፤ የማህበረ ካህናትም አባላት በጀመሩት ጸንተው ካንተ ጋራ ከመቆም ይልቅ በማይረባ ጥቅም እየተታለሉ ተበታትነው ብቻህን ብትቆምም ፤ አብረውህ ጸንተው ከቆሙት ክርስቲያኖች ጋራ እስከ አሁን ባደረከው ጥረት ከአሬንታሎች አድርሰኸዋልና በርታ። ካንተ ጋራ የሚተባበሩ ሁለት ካህናት ብታገኝ ብዙ መስራት በቻላችሁ ነበር። አንተና አብረውህ የቆሙት ክርስቲያኖች ሳትበታተኑ ጠንክራችሁ ወደ አሬንታሎች በማድረሳችሁ አቡነ ጳውሎስ ደንግጠዋል። ተሰደድን የሚሉትም ይህን ይዘው ቢነሱ ኖሮ፤ ካንዲት አጥቢያ ከናንተ ጋራ የቆሙት የኦሬንታልና የባዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከነሱ ጋራ በመቆም ከባድ ችግር ይፈጠር ነበር።

አቡነ ጳውሎስ ”ኮምኒስቱ መንግስት ከአቡነ ቴዎፍሎስ ጋራ ብዙ ጠቃሚ ሰዎችን ከመግደሉ ባሻገር፤ ብቃት የሌላቸውን ሰዎችንና ካድሬዎችን በቤተ ክርስቲያን ከተተባት፤ እኔ በእስር ቤት ብዙ ፍዳ የከፈልኩና ከሞት የተረፍኩ ነኝ። ከከንሳስ ተነስቶ ከናንተ የደረሰው ስህተት፤ በዚህ የጥፋት ዘመን በቤተ ክርስቲያናችን ከገቡት ብዙ ስህተቶች አንዱ ነው። የሰንበት ተማሪው በህዝቡ መካከል የሚያራግበው ይህንን የተሳሳተው ትምህርት ነው። የሰንበት ተማሪው ይህን ስህተት በህዝቡ ጭንቅላት ስለከተተው ለማረም የናንተን ድጋፍ እፈልጋለሁ ብለው ግብጽ ድረስ ሄደው ከፓትርያርክ ሽኖዳ ጋራ እንዲፈራረሙ ካደረጋቸው አንዱ ይህ ነው። አቡነ ጳውሎስ በደርግ ጊዜ የታየውን ድክመት በማሳየት፤ ከተወቃሽነትና ከትዝብት ራሳቸውን ለማዳን እየጠበቁ ነው።

አቡነ ጳውሎስ ከናንተ ከንሳስ ነጥሮ በአሬንታሎች ከተወረወረባቸውን ወቀሳ በዚህ ፈሊጥ ካመለጡ በኋላ ፤ በውስጥ ደግሞ ሳይገባቸውም ሆነ በተንኮል የሚያራግቡትን እንደነ ዳንዔል ያሉትን እንዲያስቆምላቸው ላቶ መለሰ ነግረው ፤ አቶ መለሰም ”ባስተዳደርና በሃይማኖት የምትገቡ ፋናቲኮች ተጠንቀቁ“ የሚል ማስጠንቀቂያ ከሰጠልን በኋላ፤ በዚህ ጉዳይ እኔም ከቢሮየ እየመጡ ከሚወረውሩብኝ ዘለፋ ፋታ አግኝቻለሁ“ ካሉኝ በኋላ “ማህበረ ካህናቱ፤ አቡነ ይስሀቅ፤ አሬንታሎችም ካንተ ጋራ ቆመው ከንሳስ ድረስ መጥተው ቀሲስ አስተርየ አልተሳሳተም ማለታቸውን እነዳንዔል ከብረት እያወቁ፤ በድፍረት ከንሳስ ድረስ መጥተው የሚያውቅህንና የምታገለግለውን ህዝብ በአንተ ላይ ቀስቅሰውና

**አስተባብረው ከመሰረትካት ከምታገለግልባት ካሳደዱህ፤ በእጃቸው ባለሁት በኔ ላይ የሚያደርሱብኝን መከራ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መመዘን መቻል አለብህ" አሉኝ።**

**ቀጠሉና "በሚደርስብህ ዘለፋ ሳትሰለች፤ መጻፍሕን ቀጥል! አታቁም! ሁሉም በቅኔ ቤት በመጽሐፍ ትርጔሜ ቤት፤ የነገረ መለኮት ንጽጽር በሚሰጥበት ከፍተኛ ትምህርት ቤት ገብተው በእውቀቱ ተነክረው ሳይወጡ፤ በማያውቁት ነገረ መለኮት ገብተው የሚዳክሩ አስመሳዮችና ሀሰተኞች ስለሆኑ፤ ውለው አድረው እርስ በርሳቸው መጣላታቸው አይቀርም። ያንጊዜ ራሳቸው እነዳንዔል ይህን ጉዳይ ማፈንዳታቸው አይቀርም። "** ብለውኝ ተሰነባብተን ተለያየን።

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ አማራጭ በማጣት እንጅ፤ በዲያቆን ዳንዔልና በጀሌዎቹ በሚደርስባቸው ስድብና ግልምጫ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ደስተኛ እንዳልነበሩ ተረድቻለሁ። **ኢትዮጵያ ደርሰው ከቤታቸው ሳይገቡ ወደመቃብር መሸኘታቸውን ሳስበው፤ እነ ዲያቆን ዳንዔል በሚያደርሱባቸው ጫና ታፍነው እንደሞቱ ነው እስካሁን የሚሰማኝ። የደረሰባቸውንም ስድብ ዘለፋና ማሳደድ ሳስበው እጅግ በጣም ይዘገንነኛል።**

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ **<u>"እራሳቸው እነዳንዔል ያፈነዱታል"</u>** እንዳሉት፤ መጀመሪያ በአባ ሠረቀና በራሳቸው በነዳንዔል ክብረት መካከል ግጭት ሲፈጠር እነ ዳንዔል ክብረት ይህንን ጉዳይ፤ አበ ሠረቀን የማጥቂያ መሳሪያ አድርገው ማንሳታቸው እጅግ በጣም ገረመኝ።

አባ ሠረቀም በከንሳስ ከተማ ያለው የዲያቆን ዳንዔል ማህበረ ሌጌዎን የከንሳስ መድኃኔዓለምን ቤተ ክርስቲያን አቡነ ማትያስ አውግዘዋታል እያሉ የሚያካሂዱባትን የሀሰት ዘመቻ እያወቁ፤ እሳቸው እስኪከሰሱበት ድረስ በጉባዔ ወስነን የላክነውን አፍነው መያዛቸው ቅር ቢያሰኘንም፤ ዘግይቶም ቢሆን አቡን ጳውሎስ በህወት እያሉ **<u>"እውነትና ንጋት"</u> በሚል መዛግብቱን ከሞላ ጎደል ሰብስበው አሳትመው በማስመረቃቸው እያመሰገንኩ፤ አሁንም መጋቤ ብሉይ ሰይፈ የተናገሩት መደገሙ እጅግ በጣም ገረመኝ። እነ ዳንዔል ክብረት ከውስጥ ሆነው ከአባ ሰረቀ ጋራ በዚህ ጉዳይ ሲካሰሱ፤ የካህናቱ ቃለ ጉባዔ ጸሀፊ ሆኖ አቡነ ማትያስን ያስደበድብ የነበረው ከፋለኝ፤ "ከማህበረ ካህናቱ ጋራ ሆኘ የክህደቱን ትምህርት ለሚያራምደው ጉባዔ ቃለ ጉባዔ ጸሐፊ ሆኘ በሰራሁት ስህተት ይቅርታ እጠይቃለሁ"** የሚል ጠልሰሞ በተነ። ይህም ቤተ ክርስቲያናችንን ተብትቦ ይዞ የሚሰለከለክባት ዘንዶ መብዛቱን ካሳዩት ክስተቶች አንዱ ነበር።

**ሰሞኑን ደግሞ አቡነ ማትያስን ቅዱስ ቅዱስ እያለ ከማህበረ ካህናቱ ጋራ ሲያዋጋ የነበረው ዳንዔል ክብረት፤ አቡነ ማትያስን ሲጣላቸው በጠንቋይ እየመሰለ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?" እያለ አቡነ ማትያስን መክሰሱን ስመለከት ንስሀ ሳይገባበት ለፈጠረው የመንፈስና ቀውስና የህሊና ስብራት ይቅርታ ሳይጠይቅ ይህን**

በማለቱ፤ ኃይል ባየለበት ራሱን የሚያሰልፍ ለቤተ ክርስቲያንም ለአገር የማይጠቅም አደገኛ ሽፍጠኝነቱን በማየቴ "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ" ብሎ ዮሐንስ የተናገረውን አውሬ መስሎ ታየኝ።

"ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?" እያለ ዲያቆን ዳንኤል ያቀረበው ዘርቅ፤ ለሰው ማጥቂያ ሆኖ ባሜሪካ ፍርድ አደባባይ ብቅ ማለቱን ስንቱ እንደተገነዘበው አላውቅም። ይህ ነገር በተከሰተ ጊዜ በስህተት የገባ ነውና ይታረም ይል የነበረውን የማህበረ ካህናቱን ጉባዔ በሊቀ መንበርነት የመሩት ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ እንደነበሩ ደጋግሜ ገልጫለሁ።

ከላይ ደጋግሜ እንደገለጽኩት፤ "መታረም የለበትም የሚል እየጠለሰመ አቡነ ማትያስን እያስፈረመ ሊቀ ሊቃውንት ይመሩት የነበረውን የማህበረ ካህናት ጉባዔ መናፍቃን ናቸው" እያለ ሰውን ሁሉ ያተራምስ የነበረው ዲያቆን ዳንዔል ነበር።

ዛሬ ሁለቱም ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህና ዲያቆን ዳንዔል አቋማቸውንና አቅጣጫቸውን ቀይረው በሌላ ጉዳይ ሳይስማሙ የተጋጩዋቸውን ወገኖች ለማጥቃት ይህንን ጉዳይ መሳሪያ ለማድረግ መሞከራቸውን ስንቱ ተመልክቶታል?

አቡነ ማትያስን ከማህበረ ካህናቱ ጋራ ሲያዋጋ የነበረው ዳንዔል ክብረት፤ አቡነ ማትያስን ሲጣላቸው በጠንቋይ መስሎ "ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?" እያለ እንደተራ ነገርና እራሱ እንዳልነበረበት አድርጎ ማቅረቡና፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህም ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸውን የሰንበት ተማሪዎችንና የሰውን የመረዳት ችሎታ እጥረት እያነበቡ ሊጎዱት በፈለጉት ሰው ላይ ወቅትና ቦታ እያዩ እንደጥይት ከሚተኩሱት ከእነ ርዕሰ ደብር አብርሃም ጋራ መሰለፋቸው፤ ሁለቱንም ዲያቆን ዳንዔልንና ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን ከሚውጠው ነገር በቀር ሌላ ማየትና ማሰብ ከማይችል ዘንዶ የማይሻሉ፤ ከሰው በታች አውርዶ ጥሏቸዋል።

ዲያቆን ዳንዔል ድሮ ከሚቃወመው ጽንፍ፤ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህም አውቀውም ሆነ ሳያውቁት ቀድሞ በሚቃወሙት ጽንፍ መሰላፋቸውን ስመለከት፤ "የሚደርስብህን ዘለፋ ሳትሰለች፤ መጻፍሕን ቀጥል ! አታቋም ! ሁሉም በቅኔ ቤት በመጽሐፍ ትርጓሜ ቤት፤ የነገረ መለኮት ንጽጽር በሚሰጥበት ከፍተኛ ትምህርት ቤት ገብተው በእውቀቱ ተነክረው ሳይወጡ፤ በማያውቁት ነገረ መለኮት ገብተው የሚዳክሩ አስመሳዮችና ሀሰተኞች ስለሆኑ፤ ውለው አድረው እርስ በርሳቸው መጣላታቸው አይቀርም። ያንጊዜ ራሳቸው እነዳንዔል ይህን ጉዳይ ማፈንዳታቸው አይቀርም" ብለው መጋቤ ብሉይ ሰይፈ የነገሩኝ ሲፈጸም ማየቴ አስደንቆኛል።

ዲያቆን ዳንዔል በአቡነ ማትያስ ላይ በነገረ ዘርቅ ያቀረበውን የተሳሳተ ትምህርት እንዲታረም፤ የማህበረ ካህናቱ ጉባዔ እንዲታረም መጠየቁ የሚያስመሰግነው እንጅ የሚያስወቅሰው አልነበረም። የሚያስወቅስ እንኳ ሆኖ ቢገኝ፤ ተወቃሾችና ተከሳሾች፤ በተንኮል ያስገቡትና ተቀባይነት እንዲኖረው ከከፈለኝ ጋራ በመተባበር በስፋት የሰበከው ራሱ ዲያቆን ዳንዔል ነው። የስህተቱ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን በገባበት ወቅት፤ ከአቡነ ይስሐቅ ጀምሮ አቡነ ማትያስም እኔም በአገር አልነበርንም። አቡነ ጳውሎስም አልነበሩም። አቡነ ጳውሎስን የወቀስናቸው፤ ለኛ በስልክ እባካችሁ በዚህ ጉዳይ አትለያዩ እያሉ፤ ማርም ሲገባቸው የፖለቲካው መርሆ ህዝብ የሚለያይበትን የሚፈጥር ይህን ሲያገኙ የበለጠ እንዲጠቀምበት እያወቁ፤ ከኦሬንታሎች ጥያቄ እስኪመጣበቸው ድረስና በአባ ሠረቀና በነ ዳንዔል ክብረት ግጭት እስኪፈነዳ ድረስ አፍነው በመያዛቸው ነው።

በዚህ ጉዳይ እርስ በርስ ከተደባደቡትና ከተዘሉፍት አንዱ አቡነ መልከ ጼዴቅ ናቸውና በዝምታ ለማለፍ በመሞከራቸው ከወቀሳ የሚያመልጡ አይደሉም። ሌላው የሚያስገርመው የገባው ስህተቱ መታረም አለበት በማለት ጥያቄ ያቀረበውን የማህበረ ካህናቱን ጉባኤ የመሩት ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህም እዚያው አዲስ አበባ ነበሩ።

ከሁሉም የበለጠና የተደራረበ ደባ የፈጸሙት ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ናቸው። በመጀመሪያ ይህ ስህተት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ሲገባ እዚያው አዲስ አበባ ነበሩ፤ መግባቱን ያውቃሉ ተሸክመውት ወደ አሜሪካ ገቡ። በከንሳስ ፈንድቶ እንዲታረም የጠየቀውን ጉባዔ የመሩት እራሳቸው ናቸው። እንዲታረም የጠየቁትን የስህተት ትምህርት ርእሰ ደብር ጠልሰሞ ሲያቀርብ ከነ ዶ ክተር አክሊሉ ጋር ሆነው መረቁት። ሊቀ ማእምራን የተሳሳተ ጠልሰም ነውና ለህዝብ እንዳይሰራጭ ብለው ሲያግዱት አብረው ተስማምተው አገዱት። እንደገና ከባለ አደራ ቦርድና ከሊቀ ማእምራን አማረ ጋራ በሌላ ነገር ሲጋጩ፤ የተሳሳተ ጠልሰም ነው ብለው ካሳገዱበት ከርእሰ ደብር አብርሃም ጋራ በመወገን፤ አስተርአየና ሊቀ ማእምራን የተወገዙ ናቸው የሚለውን የደፍተሮችን ጉባዔ መሩ። ለክሳቸው ማዳበሪያ ና መፈራረጃ አድርገው ለዳኛ አቀረቡት። ታዲያ ከዚህ የከፋ ተስለክላኪ ዘንዶነት ምን አለ?

ዲያቆን ዳንኤል ደግሞ፤ ማህበረ ካህናቱንና አቡነ ማትያስን እንዲጋዋገበት "ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?"እያለ በነገረ ዘርቅ በአቡነ ማትያስ ላይ ሲያቀርበው፤ አንተ አሽሙረኛ፤ ነገረ ስሪና ዘርቀኛ እረፍ መባል አይገባውም? በዚህ አይነት ነገረ ዘርቅ የሚጠይቀው ማንን ነው? ራሳቸውን አቡነ ማትያስን ነው?ወይስ በከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን መሽገው፤ አቡነ ማትያስ የከንሳስ መድኃኔዓለምን ቤተ ክርስቲያን አውግዘዋል እያሉ የከተማውን ህዝብ በሀሰት የሚያምሱትን ነው? ወይስ እሱ ያልተባበረበት ከኦሬንታል ማህበር የሚያወጣ አቡነ ማትያስ ብቻቸውን ያደረጉት ሌላ ስህተት አለ? በቆዩ ቁጥር እንዲህ የመሳሰሉ ደባወችን

የሚፈጽሙት ሰዎች "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ" ብሎ ከመገሰጽ ችላ ብሎ እነሱን መከተል ተገቢ ነው?

ኃይል ካለው ጎን ተሰልፎ፤ ሊጎዱት የማይችሉ መሆናቸውን እያጠና ፤ራሱ የሰራውን ስህተት ገልብጦና መልኩን ቀይሮ፤ በዚህ መልክ ከሚያቀርብ ከዲያቆን ዳንዔል ጋራ መሰለፍ፤ እንኳን "እውነቱን እውነት፤ ውሸቱን ውሸት" በሉ እያለች ለምታስተምር ቤተ ክርስቲያን፤ ለታትክቲክና ለዘዴ እየተባለ በገሀድ የሚዋሸውን ማስተናገድ ለፖለቲካም አይጠቅምም።

አቡነ ማትያስ የብእር ሰው እንዳልሆኑ እያወቅን በጠንቋይ እየመሰለ "ብእር አነሱ" እያለ ያቀረበልንን ዘርቅ ይበል ብሎ መቀበል፤ በእምነቱ መቀለድና የሚታዘብ ሰው እንደሌላ ማድረግ እጽፍ ድርብ በደል ነው። የተዋህዶ ነገረ መለኮት ትምህርት አይቀበለውም። የብዕር ሰው እንዳልሆኑ የምናውቃቸውን አቡነ ማትያስን ከጠንቋይ ጋራ እያመሳሰለ ካቀረባቸው፤ ይህን ሁሉ ጉድ የፈጸመው ዲያቆ ን ዳንዔል ራሱን ምን ብሎ ሊሰይም ነው? በተሳሳተበት ጉዳይ የጎዳውን ሰው ይቅር በሉኝ ሳይል፤ ንስሀ ሳይገባበትና የራሱን አቋም ሳይገልጽ ሌላውን መንቀፍ መዝለፍና ባሽሙር መናገር "ዘያነብብ ንባበ ጽሩአ ያገብኡ ሎቱ በእለተ ደይን" የሚለው ክርስቶስ ይፈረዳዋል።

በዚህ ጉዳይ የእኔ ሚና ምን መሆን አለበት? ብየ ራሴን እንድጠይቅ ተገደድኩ። "አንድነ ሰው ነፍጠኛ ለመባል ወይም ከነፍጠኛ ደራጃ ላይ የሚያደርሰው፤ በሚተኩሳት ጥይት የተጠመጠመውን ዘንዶ፤ ከተጠመጠመበት ሰው ለይቶ መምታት ከሚያስችለው ትኩረት ላይ ሲደርስ ብቻ ነው" እንደሚሉት የኔን ትኩረት ለመፈተሽ ከምገደድበት ላይ የደረስኩ መሰለኝ። "ብእር ቀርጾ፤ ብራና ፍቆና ቀለም በጥብጦ የሚጽፍም ጸሐፊ የዘንዶ ባህርያ ያለውን ሰው ከተጠመጠመበት ለይቶ የማቅረብ ብቃት ከሌለው ጠልሰመኛ እንጅ ጸሐፊ አይባልም" ብለው መምህሮቼ በትርጓሚያቸው ሲያትቱ የሰማሁትም መንፈሴን በረበረው።

አቡነ ማትያስ የሚወቀሱበት "በስህተት የገባ ነው እንዲታረም ይተባበሩን" ብለው እነ አቡነ ገብርኤል ሲለምኗቸው፤ በወቅቱ ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ ቀኝ እጅ ሆነው ይራወጡ የነበሩትን የእነ ዲያቆን ዳንንኤል ምክር በመስማት የማህበረ ካህናቱን ጥያቄ ባለመቀበላቸው እንጅ፤ "ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?" እያለ ዲያቆን ዳንዔል ባቀረበው ሀሳብ አቡነ ማትያስን እንደ ጠንቋይ ብእር አነሱ እያለ ያቀረበውን ዘርቅ መቀበል ቀርቶ ስሰማው ዘገነነኝ። ታዲያ በዚህ ጉዳይ ከአቡነ ማትያስ ጋራ ወይስ ከዳንዔል ጋር መሰለፍ አለብኝ? ፈጽሞ የለብኝም። "ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ " የሚለውን ያስተማሩኝ

ሊቃውንት፤ በየምግባሩና በየስራው ለመግለጽ እንጅ፤ በሌላ ነገር የበደለ ቢሆንም ባልደለበት ነገር፤ በሽረኛ ሲገደል ታደገው እንጅ፤ እሰይ እንኳ ብለህ ብትስማማ አንተም ነፍሰ ገዳይ ነህ“ ብለው ያስተማሩኝን እንዴት ልለፈው?

በፊላው ራሱን ደብቆ በረግረግ ቦታ ራሱን ደብቶ ያገኘውን እንደሚውጥ ዘንዶ፤ ዲያቆን ዳንዔልም በቅዱሳን ስም ተደራጅተው በገጠር በከተማ እየተዘዋወሩ በየዋህነት በቅን ልቡና በመፈተን ላይ ያለችውን ቤተ ክርስቲያችን በመታደግ ባሉት ወጣቶች ራሱን ሸፍኖ፤ ራሱን ለመቀለብ በነገረ ዘርቁ ሰውን እንደሚውጥ ተረድቸዋለሁ። ማህበረ ቅዱሳንን ፈላ፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ረግረግ አድርጎ ለራሱ ህልውና ብቻ እየተጠነቀቀ ሰው የሚጎዳ ነው። እንደ እነ አቶ ኤርምያስ ለገሰ ንስህ ገብቶ የራሱን አቋም ግልጽ አድርጎ ካላቀረበ፤ ከእንግዲ ወዲህ የሚጠለስመውንና የሚናገራቸውን ብቻ ሳይሆን፤ ወደፊት የሚጠለስማቸውንና የሚናገራቸውን ለቤተ ክርስቲያን ብሎ ያደርገዋል ብየ አላምንም።

**በዚህ ጉዳይ ከአቡነ ማትያስ ይልቅ፤ ሽንጡን ገትሮ በሊቃውንቱ ሁሉ የዘመተ ዲቆያቆን ዳንኤል ነው። በከፈተው በዘንዶው አፍ የነፍጡን ጫፍ አስተካክሎ እንደከተተው፤ <u>“ለመሆኑ የእኛ አባት የቱን ነው እየፈጸሙ ያሉት? ወይስ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውጭ ሆነናል?”</u> እያለ ነገረ ዘርቅ ለመናገር በከፈተው አፉ፤ ዘርቀኛነቱን የተረዳ የራሱን አንደበት አንተርሶ የመሳሰሉ ጦማሮች በሊቅበት፤ ተገቢ አይደለም ሊል የሚችል ይኖራል?**

***“ወእምዝ ወጽአ ካልዕ አርዌ እምነ ምድር፤ ወበሥልጣኑ ለቀዳማዊ አርዌ ይገብር ኵሎ በቅድሜሁ፤ ወይረስያ ለምድር ከመ እለ ይነብሩ ውስቴታ ይሰግዱ ሎቱ ለቀዳማዊ አርዌ ”* (13፡12) ማለትም፡- ከምድር ሲወጣ ያየሁት ሌላው አውሬ፤ ከቀደመው ከትልቁ <u>አውሬ</u> ባገኘው ስልጣን፤ በምድር ላይ ያለ ሰው ሁሉ ለቀደመው አውሬ እንዲሰግድለት ያደርጋል” ብሎ ዮሐንስ በራእዩ እንደገለጸው፤ ዲያቆን ዳንዔልም ቤተ ክርስቲያንን እያሸና እያደቀቀ ከሚውጠው ከታላቁ ተስለክላኪው ዘንዶ ከወያኔ ባገኘው ስልጣን፤ በነገረ ዘርቁ ህዝቡን ለወያኔ ለማሰገድ የሚያደርገው ጥረት እንጅ፤ ዲያቆን ዳንዔል ይህን የሚያደርገው ለቤተ ክርስቲያን ብሎ ነው የሚል ካለ፤ ዘንዶው ከሚስለከለክበት ከአባይ ፊላና ከረግረጉ ቦታ ያልተሻልክ ማስብ የማትችል ነህ ቢባል የሚስማማው ይመስለኛል። በበኩሌ <u>“ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ”</u> ጉድ ነው ፣ከማለት በቀር፤ ዲያቆን ዳንዔል በአቡነ ማትያስ ላይ ብቻ በማሸከም የሚያቀርበውን ዘርቅ አሜን ብየ ለመቀበል፤ ከኦርቶዶክስ ትምህርተ ለኮትና ከ ኦርቶዶክሳዊት ቅስና ጋራ የተወሀደችው ሕሊናየ አትፈቅድልኝም። <u>ይቀጥላል።</u>**